ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

Solidarity Movement for a New Ethiopia

---

## የታቀደው የኢትዮጵያ ጉዳየኞች የትብብር ስብሰባ ጥሪ ተሰርዟል!

ከጥቂት ሣምንታት በፊት ለአዲሲቷ የጋራ ንቅናቄ የኢትዮጵያ ጉዳይ ያገባኛል ፣ ይመለከተኛል የሚሉ ጉዳየኞች በአንድ ቦታ ተሰባስበው የአገራችንን ጉዳይ በተመለከተ የሚመክሩበትን መድረክ ለማመቻቸትና መንገዱን ለመጥረግ የሚያግዝ ጉባኤ ለማድረግ **ለመገናኛ ብዙሐን (የፓልቶክ ክፍሎችንም ጨምር) ፣ ለፖለቲካ ድርጅቶች ፣ ለእርነት ንቅናቄዎች ፣ ለሲቪክ ድርጅቶች ፣ ለሴቶችንና ወጣቶች ማኀበራት ፣ ለሃይማኖት ድርጅቶች እንዲሁም ለአገር ሽማግሌዎችን እና ሌሎች ለአገራችን ቅን የሚያስቡና ለነጻነቷ የሚታገሉ** ሁሉ ጥሪ ማቅረባችን ይታወሳል፡፡ ንቅናቄው ይህንን ጥሪ ባስተላለፈበት ወቅት የማስተባበር ኃላፊነቱ የወሰደ በመሆኑ ጥሪው ለሁሉም ወገኖች እንዲደርስ በመደረጉ በተለያዩ የመገናኛ አውታሮች – በድረገጾች ፣ በፓልቶክ የመወያያ ክፍሎች ፣ ወዘተ በጉዳዩ ላይ የጠለቀ ወይይት አንዳንዴም ክርክር ሲካሄድበት ሰንብቷል፡፡

ሆኖም ግን ጥሪው ከተካሄደበት ቀን ጀምሮ እስካሁን የየትኛወም የፖለቲካ ድርጅት ምላሽ ያልሰጠ ሲሆን ጥቂት የሲቪክ ድርጅቶች ግን ያላቸውን ድጋፍና ፈቃደኝነት ገልጸውልናል፡፡ ከሁሉ በላይ ግን ከህዝቡ ያገኘነው አበረታችና በጎ ምላሽ ከፖለቲካ ድርጅቶች ይልቅ ህዝባችን ለትብብር ምን ያህል ፍላጎት እንዳለው ያሳየበት መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ሳንጠቅስ የማናልፈው ሐቅ ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት በአገራችን ከምንግዜውም በበለጠ ሁኔታ የሰብዓዊ መብት ጥሰት ፣ አፈና፣ ግድያ፣ እስራት፣ ወዘተ እየተባባሰ የመጣበት መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ ባለፈው ተካሄደ በተባለው <<ምርጫ>> ህወሃት/ኢህአዴግ 99.6 አሸነፍኩ ብሎ ሁሉንም የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከፖለቲካ እንቅስቃሴ አስወግዶና የፖለቲካ ምህዳሩን ዘግቶ ባለበት ወቅት በኢትዮጵያ ጉዳይ ላይ ያገባኛል የሚሉ ሁሉ ሊተባበሩ አብረው ሊሠሩ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ከሃዘንና ምሬታችን ወስጥ ያገኘነው ጣፋጭ አጋጣሚ መሆኑ ለሁላችንም ግልጽ ነው፡፡ ሆኖም ግን ይህንን አጋጣሚ ተጠቅሞ ኃይላችንን ከማስተባበር ይልቅ – በተለይ የፖለቲካ ድርጅቶች – ለዘመናት ጠፍሮ በያዛቸው የዓምባገነንነት አባዜ ተወጥረዉ የጎሪጥ እየተያዩ እርስበርሳቸው በማጠላለፍና በመካሰስ ለመቀጠል ሚፈለጋቸው <<በእርግጥ እየታገሉ ያሉት ማንን ነው>> ብለን እንድንጠይቅ አድርጎናል፡፡ ለቀረበው ጥሪ አዎንታዊም ይሁን አሉታዊ ምላስ ለማስጠት አለሚፈለጉ ለመተባበርና አብሮ ለመሥራት ራሣችን ችግር እንዳለብን በራሱ የሚጠቁም ሲሆን፤ ይህም ችግር የመጣብን ከሌሎች ጋር መተባበር የእኛን ኃይል የሚያዳክምና የሌላውን የሚያጎለብት ማስሎ ስለሚታየን፤ እንዲሁም ሌሎች በትግሉ ወስጥ ያሉትን ወገኖች የጋራ ሀገራዊ ጥቅም ተካፋይ አድርጎ ከመመልከት ይልቅ ተቀናቃኝ ባላንጣ አድርገን በሚፈረጃችን ነው፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ጠባብ አመላካከት በተኮፈሱ ድርጅቶችና መሪዎች ቅኝት ትግላችን የትም መድረስ እንደማይችል የተገነዘቡ የፖለቲካ መሪዎች ስለመኖራቸዉ ጥያቄውን ለራሳቸው እንድንተወው አስገድዶናል፡፡ በበኩላችን ተቀራርቦ ላለመጋገርና ላለመተባበር ምክንያት ተብለው ከሚጠቀሱትም ሆነ ከሌሎች ሰንካላ አስተሳሰቦች አኳያ የእያንዳንዱ ፖለቲካም ሆነ የሌላ ድርጅት አባል እንዲሁም ሕዝቡ ባጠቃላይ ለመተባበር እንቅፋት የሆኑበትን ድርጅቶችና መሪዎች በግልጽ ሊተቻቸው ፣ ሊያጋልጣቸወና በኃላፊነት ሊጠይቃቸው ይገባል እንላለን፡፡ <<ከጎሣ ይልቅ ሰብዓዊነት>> የቀደመባትን አዲሲቷን ኢትዮጵያ እንመሠርታለን ብለን የምናስብ ከሆነ በአዲስ አስተሳሰብ መሳትና ችግሮቻችንን በግልጽ አንስተን መወያየትና መተቻቸት አለብን፡፡ ይህም ከራሣችን ጀምሮ እስከ መሪዎቻችን ድረስ ሊዘልቅ ይገባል፡፡

ምንም እንኳን ንቅናቄያችን ጥሪ ካቀረበላቸው ጉዳየኞች በተለይም ከፖለቲካ ድርጅቶችና የግምባር ንቅናቄዎች አጥጋቢ ምላሽ ባለማግኘቱ በቅርቡ ለማድረግ ያሰብነውን ታላቅ የትብብር ስብሰባ የሰረዘ መሆኑን ቢያስታውቅም በቀጣይነት ይህንን የትብብር መድረክ ለመፍጠር የሚያደርገውን ጥረት እንደማያቋርጥ ለማሳሰብ እንወዳለን፡፡ በተለይም ለዓመታት ከፖለቲካውና አገራዊ ጉዳዮች ተገልለው የኖሩ የወጣቶችን እንዲሁም የሴቶችና የሃይማኖት ድርጅቶችን የማስተባበር ሂደት ንቅናቄአችን በትጋት ለመቀጠል ቆርጦ መነሳቱን ለመግለጽ ይወዳል፡፡ ከዚህ አኳያ በቅርቡ እየተቋቋሙ ያሉ የወጣት ፤ ሴቶችና ሌሎች ድርጅቶች የምናበረታታ ሲሆን፤ በቅርቡ የኦሮሞና የአፋር ድርጅቶች ትብብርን አስመልክቶ ያወጡትን መግለጫ የምንደግፍ መሆናችንና ሌሎችም ድርጅቶችና ንቅናቄዎችም ይህንን ፈለግ እንዲከተሉ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

በመጨረሻም ንቅናቄያችን የጀመረውን የትብብር መድረክ ለመፍጠር በሚያደርገዉ ጥረት ተመሳሳይ ተግባር የጀመሩና ወደፊት ለመጀመር ከሚያስቡ ጋር ተባብረን ለመሥራት ያለንን ፍላጎት በድጋሚ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡ ለዚህም ወገንን የማዳን ጥሪ አፋጣኝ ምላሽ በማስጠት ሕዝባችን ለዘመናት ሲናፍቀው የኖረውን ነጻነት ዕውን በማድረግ ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለመላው የአፍሪካ ቀንድ ዘላቂ ሰላም ሊያስገኝ በሚችል ተግባር ሁላችንም ቀና ውሳኔ ለማድረግ እንድንችል ፈጣሪያችን ይርዳን፡፡

ከአክብሮት ሰላምታ ጋር



አባንግ ሜቶ
ዋና ዳይሬክተር
ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

*******************************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ **የንቅናቄውን የዕርቅ ግብረኃይል** በ (reconciliation@solidaritymovement.org) ወይም ዋና ዳይሬክተሩን ለአቶ አባንግ ሜቶ (obang@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለማግኘት ይችላሉ፡፡*

